ልደታ ካቶሊክ ካቴድራል ት/ቤት ሚያዝያ 21 / 2012 ዓ.ም

የትምህርት ዓይነት አካባቢ ሳይንስ
3ኛ ክፍለ ጊዜ አካባቢ ሰይንስ ትምህርት የትምህርት መካካሻ ጥያቄዎች
ክፍል 3ኛ
<u>መልመጃ</u>

<u>ምዕራፍ ሶስት</u>
<u>ርዕስ የንብ እርባታ</u>

ንብ ጠቃሚ ከሆኑ ነፍሳት ተመደባለች :: ንብ ማርን በመስራት ለሰው ልጅ ከፍተኛ ጥቅም ትሰጣለች::

ማር በዘመናዊና በባህላዊ ዘዴ ይመረታል :: ዘመናዊ የንብ ዕርባታ ፣ ባህላዊ የንብ ዕርባታ ዘዴ የተሻለ የምት መጠንና ጥራት ያለው ማር ለማግኘት ያስችላል ::

ንቦች ከአበባ ቀሰምን በመሰብሰብ ማር ይሰራሉ :: ንቦች በሶስት ይከፈላሉ

<u>እነሱም:</u> 1. ንግስት ንቦች

2. አውራ ንቦች

3. ሰራተኛ ንቦች ይባላሉ

ንቦች እያንዳአንዳቸው የራሳቸው የስራ ድርሻ አላቸው :: የህይወት ኡደታቸው ከእንቁ ላላቸው በመጀመር ቀስ በቀስ ወደ እጭነት፣ ከእጭነት ወደ ሙሽሬነት ፣ በመጨረሻም ከሙሽሬነት ወደ ጉልምስና ንብነት ወደ ጉልምስ ንብነት ያድጋሉ ::

ንቦች የሚከተሉትን የሰውነት ክፍሎች አሏቸው :: <u>እነሱም</u> 1. አይን 2 ሶስት ጥንድ እግሮች አንድ ጥንድ ክንፍ ናቸው ::

<u>*የንብ ሊይነት ክፍል*</u>

1. <u>ንግስት ንብ</u> በመጠን ከሰራተኛ ንብ ተለቅ ያለች ስትሆን ከአውራው ንብ ታንሳለች :: የሰውነትዋ ቁመት ከሰራተኛ ንብ ይረዝማል ክንፎችዋ አጫጭር ናቸው ::
2. <u>አውራ ንብ</u>፡ በመጠን መካከለኛ ነው ::
3. <u>ሰራተኛ ንብ</u> : አጭር ወፈርና አነስ ያለ መጠን አላቸው ፣ ረዣዥም ክንድ አላቸው ::

<u>ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ ከሆኑ እውነት ከልሆኑ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ</u>

_____ 1. ንቦች ማርን የሚሰሩት ከአበባ ቀስም በመሰብሰብ ነው ::

_____ 2. ንቦች ሶስት የሰውነት ክፍሎች አሏቸው ::

_____ 3. ንቦች እንቁላላቸውን የሚጥሉት በቆሻሻ ስፍራ ላይ ነው ::

_____ 4. ማርን በሁለት ዘዴ ማምረት ይቻላል ::

_____ 5. ንቦች የእያንዳአንዳቸው የስራ ድርሻ አላቸው ::

_____ 6. ከባህላዊ የንብ እርባታ ዘዴ ጥራት ያለው ማር በዘመናዊው ዘዴ ይበልጥ ማግኘት ይቻለል ::

_____ 7. ንብ በጣም ጎጂ ከሆኑ ነፍሳት መካከል ትመደባለች ::

_____ 8. የንቦች የህይወት ኡደት የሚጀመረው የእጭነት ነው ::

_____ 9. የንብ ኡደት ህይወት አራት ደረጃዎች አሉት ::

_____ 10. ንቦች ስኳርን በማምረት በጣም ብዙ ጥቅሞች ይሰጡናል ::

2. ርልስ፡ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ውጤቶች

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተለያዩ ምርቶች የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ይገኛሉ :: እነዚህ ምርቶች የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶች ፣ የቆዳ ውጤቶች ፣ የእንጨት ውጤቶች የታሸጉ ምግቦች የኬሚካል ውጠቶች እና የመሳሰሉት ናቸው :: እነዚህ ምርቶችም ከአምራቾች ወደ ተጠቃሚቆች በነጋዴዎች በኩል ይሰራጫሉ

የንግድ አይነቶች ሶስት ናቸው

1. አስመጪና ላኪ 2 የጅምላ ንግድ እና 3 የችርቻሮ ንግድ ናቸው ::

1. የአስመጪና ላኪ ንግድ : ከሀገር ውጭ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማስመጣትና ወደ ውጪ በመላክ የሚታወቅ ንግድ ነው ::

2. የጅምላ ንግድ፡ ማለት ደግሞ አምራቾች ምርትን ለነጋዴ በብዛት በመሸጥ ወይንም ነጋዴዎች ከአምራቾች ላይ በመግዛት ለችርቻሪዎች በብዛት የሚሸጡበት ሁኔታ ነው :: በዚህ ምክንያት ተጠቃሚው ህብረተሰብ ከጅምላ ፣ ነጋዴዎች ሸቀጥን ገዝተው መጠቀም ባለመቻላቸው

3. ችርቻሮ ንግድ፡ ሸቀጥን ከጅምላ ነጋዴ በመግዛት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚደርስበት የንግድ ስርአት ነው ::

በዚህ የንግድ ሂደት በአምራቾች ፣ በአካፋፋዮችና በችርቻሪዎች መካከል ቁርኝትና መደጋገፍ ይታያል:: ከአምራቾች ምርት ካላቀረቡ አካፋፋዮች ምርት አያገኙም :: አካፋፋዮች ምርት ካላገኙ ችርቻሪዎች ለህብረተሰቡ የሚያቀርቡት ነገር አይኖራቸውም :: ስለዚህ ህብረተሰቡ ለፍጆታው የሚፈልገውን ሸቀጥ ማግኘት አይችልም :: ይህ ትስስር በገዢዎችና በሻጮች መካከል ያለውን መደጋገፍ ያሳያል ::

ለ. በ"ሀ" ክፍል ያሉትን ከ"ለ" ክፍል የሚገኙን አዛምዱ

ሀ	ለ
_____ 11. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚመረት	ሀ. ሶስት
_____ 12. ለመቆፈሪያነት የሚያገለግል መሳሪያ	ለ. በአገራችን ይመረታሉ
_____ 13. ከሀገር ውጭ ምርትን በማምጣት ወደ ውጭ መላክ	ሐ. የቆዳ ውጤት
_____ 14. የንግድ አይነቶ	መ. ዶማ
_____ 15. አምራቾች ምርት ካላቀረቡ	ሠ. እካፋፋዮች ምርት አያገኙም
_____ 16. የህንጻ መሳሪያ ማምረቻዎች	ረ. የጅምላ ንግድ
	ሰ. አምስት